

# የሲያትል የማመላለሻ ፍትሃዊነት ማዕቀፍ

## የማህበረሰብ የስራ ቡድን የበለጠ ፍትሃዊ እና እኩልነት የሚታይበት የመጓጓዣ የወደፊት ፈንታ የግንባታ መንገዱን ይመራል።

ተቋማዊ ዘረኝነት በማመላለሻ ስርዓታችን ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል፣ እናም በቁም ነገር እሱን ለማጥፋት ሚናችንን እንወስዳለን። በማመላለሻ የአቋም መመሪያ እና አሰራሮች ውስጥ በተለምዶ የማይሰሙ የማህበረሰብ ድምፆችን ከፍ ማድረግ ወሳኝ ፍላጎት ነው። ከ2019 ጀምሮ፣ ግብዓቶችን መድበናል እና ከ11 የማህበረሰብ አባላት ጋር ተባብረናል እና አሁን በፍትሃዊነት ላይ ያተኮሩ ከ200 በላይ ስልቶች ያለው ማዕቀፍ አለን። አባላት ጥቁር፣ ተወላጆች፣ እና የቀለም ሰዎች እና ተጋላጭ ማህበረሰቦችን ይወክላሉ። በሲያትል-ኪንግ ካውንቲ ክልል ውስጥ ካሉ የአካባቢ ድርጅቶች ጋር የተገናኙ ናቸው እና ልምዳቸውን እና ከመጓጓዣ ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶች እንዲፈቱ እርምጃዎችን ለመለየት ሙያዊ እውቀታቸውን ይተገብራሉ። የሚገኘው የማዕቀፍ እሴት የሲያትል የማመላለሻ መምሪያ (SDOT) ሰራተኞችን ተግባር ለመጪዎቹ አመታት ይመራል። በሲያትል ከተማ ውስጥ ዘርን እና ማህበራዊ ፍትኀዊነትን ማዕከል ለማድረግ እኛ በስራ ቡድኑ ቁርጠኝነት እና አስተዋጾ ተከብረናል።

### ፍላጎት

የዘረኝነት የአቋም መመሪያዎች እና የመዋዕለ ንዋይ ንፍገት ታሪክ በማመላለሻ ስርዓታችን ላይ ኢፍትሃዊነትን ፈጥሯል። የረዥም ጊዜ የዘረኝነት ተጽእኖ የሀብት መዳረሻን እና እድሎችን ይገድባል። ውጤቶቹ በመፈናቀላቸው እና ብዙ ጊዜ ዝቅተኛ ጥራት ባለው የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ተደራሽነት ምክንያት የቀለም ማኅበረሰቦች ከነጭ አቻዎቻቸው ይልቅ ረዘም ያሉ ጉዞዎች መውሰዳቸውን ያካትታል። ቀለም ያላቸው ማህበረሰቦች ለብክለት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ አነስተኛ ቢሆንም፣ ተመጣጣኝ ባልሆነ ሁኔታ ተጽኖዎቹን ይለማመዳሉ። ይህንን አዲስ ማዕቀፍ ወደ መምሪያ የአቋም መመሪያዎች እና አሠራሮች ማካተት ማለት እነዚህን ጥያቄዎች ለመፍታት አንድ እርምጃ ነው።

---

**እኩልነት በዘር፣ በፆታ፣ በመደብ/ክፍል እና በሌሎች ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ተሻግሮ የፍትሃዊ አያያዝ፣ እድሎች እና ውጤቶች መለኪያ ነው።**

---

**የመገናኛ መረጃ**: (206) 684-5142 |transportequity@seattle.gov
seattle.gov/transportation/EquityFramework

Seattle Department of Transportation

## ማዕቀፍ

ማዕቀፉ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሰነድ ነው። በአፈጻጸም ዕቅዱ ውስጥ ያሉትን ዘዴዎች የሚመሩ እሴቶችን እና ስልቶችን ይገልፃል። የትግበራ እቅዱ ከ2022 እስከ 2028 የሚዘረጋ በመሆኑ፣ በየጊዜው የሚስተካከል፣ በቅርብ ክትትል የሚደረግበት እና በመደበኛነት የሚዘመን ድርጊታዊ ሰነድ መሆኑን መረዳት ነው።

ከመምሪያው ስድስት እሴቶች አንዱ በመሆኑ፣ ማዕቀፉ ፍትሃዊነትን ለማምጣት ወሳኝ መሳሪያ ነው። ግባችን የዘር እኩልነት የሰፈነበት እና ማህበራዊ ፍትህ የሰፈነበት የማመላለሻ ሥርዐት ለመገንባት ከማህበረሰቦች ጋር አጋርነት መመስረት ነው።

ማን በስራ ቡድኑ ውስጥ እንዳለ፣ ስራችንን ስለሚመሩት እሴቶች እና ስልቶች ለማንበብ፣ እና በሚቀጥሉት ጥቂት አመታት ውስጥ ስለምናተኩርባቸው ስልቶች የበለጠ ለማወቅ የእኛን ድኅረ-ገጽ በ seattle.gov/transportation/EquityFramework ላይ ይጎብኙ።

በተቋማት የተሰሰገ ዘረኝነት ብዙውን ጊዜ ባለማጤን ወይም በድንገት ሳይታወቅ በቀለም ሰዎች ጉዳት ዋጋ የሚሆኑ ለነጭ ሰዎች ጥቅም የሚሠሩ ድርጅታዊ መርሃግብሮች፣ የአቋም መመሪያዎች ወይም ሂደቶች ናቸው።

## የመጓጓዣ እኩልነት ማዕቀፍ




**የተጠቀሱ ምንጮች:**
https://ehp.niehs.nih.gov/doi/10.1289/EHP959
www.pnas.org/content/116/13/6001
www.ncbi.nlm.nih.gov/pmc/articles/PMC7037907/
www.washington.edu/news/2021/04/28/people-of-color-hardest-hit-by-air-pollution from-nearly-all-sources/